የሰበር መ/ቁ. 29920

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የባህርዳር ጨ/ጨ/አ/ማኀበር - ነ/ፈጅ ኃ/የሱስ ደምሴ - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አመሸ ሰይድ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ከነበርኩበት የሥራ ደረጃ ያለአግባብ ዝቅ የተደረግሁ ስለሆነ በደረጃዬ እንድመደብ ይወሰንልኝ የሚል ክስ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በአመልካች በኩል የቀረበን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ የኋላ ክፍያ ሣይጠይቅ በጠየቀው የሥራ መደብ ተመድቦ እንዲሰራ በማለት ውሣኔ ሠጥቶ በዚህ ውሣኔ ላይ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ቅሬታ አድሮባቸው በየበኩላቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለምዓራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ሁለቱም የይግባኝ መዝገቦች ተጣምረው እንዲታዩ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ በተመለከተ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አሻሽሎ ይ/ባይ በደረጃ 9 ከተመደበበት ቀን ጀምሮ ያለውን ክፍያ መ/ሰጭ ሊከፍለው ይገባል የሚል ውሣኔ በመስጠቱና አመልካች በበኩሉ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ምንም ሣይባል በመታለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ቀደም ሲል ክሱን ለወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው



የአሠሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ ነው በማለቱ ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ አቅርቦ ጉዳዩ እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ተጠሪ በድጋሚ ክሱን ለወረዳ ፍ/ቤት ሲያቀርብ አመልካች ያነሣው የይርጋ ክርክር ተቀባይነት ሣያገኝ መቅረቱ ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ወይንስ አልሆነም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ ከላይ የተመለከተውን ክስ ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ሲያቀርብ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር የተፈፀመው በ1994 ዓ.ም ሲሆን ክሱ ግን የቀረበው በ1998 ዓ.ም ከ4 ዓመት በኋላ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የመጀመያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍ/ቤትም ጉደዩ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ክርክሩ የግል የሥራ ክርክር እንጂ የወል የሥራ ክርክር ስላልሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው በማለት ውሣኔ የሰጠ ስለሆነ መቃወሚያው በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሣሽ የሆነ ወገን ክሱን ለፍ/ቤት ከማቅረቡ በፊት የትኛው ፍ/ቤት ክሱን ለማየት የግዛትና የሥረ ነገር ሥልጣን እንዳለው አጣርቶ ማቅረብ እንዳለበት ይታመናል፡፡ በዚሁ መሠረትም ተጠሪ ክሱን በቅድሚያ ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ጉደዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ሲል ከሣሹ/ተጠሪ/ የመረጠው ይግባኝ ማለትን ሣይሆን ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ወሣኝ ቦርድ ማቅረብን በመሆኑ በዚሁ መሠረት ክሱን ለቦርዱ አቅረቦ ክርክሩ ቀጥሎ መጨረሻ ጉዳዩ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ችሎቱም የዚህ ዓይነት ክርክር በወል የሥራ ክርክር ሊሸፈን ስለማይችል ቦርዱ ይህን ጉዳይ ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠው ሥልጣን ሣይኖረው ነው በማለት የበኩሉን ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኂላ ተጠሪ ክሱን ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ሲያቀርብ ክሱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን በመግለጽ አመልካች የይርጋ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ከሥራ ክርክር ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክስ የይርጋ ጊዜ ከፍተኛው 1 ዓመት እንደሆነ በአሠሪና ሠራተኛ አ/ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት ተጠሪ በቅድሚያ ክሱን ለወረዳ ፍ/ቤት አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን ሣይቀበል ሲቀር ክርክሩ የግል የሥራ ክርክር ከመሆኑ አኳያ በይግባኝ ሥነ ሥርዓት በመጠቀም ይህንኑ ውሣኔ ተጠሪ ማስለወጥ ሲገባው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ለሌለው ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ማቅረብ አልነበረበትም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁ 15722 ግራ ቀኙን አከራክሮ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንፃር ይህንን ጉዳይ ለማየት የሥረ - ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ውሣኔ ከመስጠቱ በስተቀር አስቀድሞ ክርክሩ በተጀመረበት በባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ክርክሩ ይቀጥል በማለት ውሣኔ አልሰጠም፡፡

ስለሆነም ለባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ድጋሚ ክስ ሲቀርብ በሕጉ ላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ ከ4 ዓመት በኂላ ቀርቦ ባለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ የይርጋ መቃወሚያውን ሊቀበለው ሲገባ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡት ይግባኝ ተጣምሮ እንደሚታይ ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም በተጠሪ በኩል የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ ከመወሰኑ በስተቀር የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ሣይመለከተው አልፎታል፡፡

ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታለፈ እንደሆነ እንደተከለከለ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5(3) ላይ የተመለከተ ስለሆነ



በዚህም ጉዳይ ይርጋን አስመልክቶ አመልካች ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ቅሬታ ስለታለፈ እንደተከለከለ የሚቆጠር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የባህርዳር ወረዳ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚሁ ጉዳይ መጋቢት 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ክሱ ያቀረበው በሕጉ ላይ የተቀመጠው ጊዜ ካለፈ በኂላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ